**<u>አደባባይ ሰልፍ ወጣሁኝ</u>**

*እምነት እሰተዳር*

ባያድለኝ ባይሆንልኝ ታንክ በድንጋይ ባልገጥም፣
ሳንጃ በፊቴ ተወድሮ ደረቴን ባልገለብጥም፣
አይን ላይን ባልተያይ ከግፍና ከጭካኔ፣
የፍልሚያው ግለት ተሰምቶኝ የታጋይኛው ወኔ፣
ለአየሩ ለህዋው አቤት ልል ቀለም ወረቀት ላይ ለቅልቄ፣
መፈክሬን አንጠልጥየ ከመሰሎቼ ጋር ተደብልቄ፣
ድንጋይ መወርወር ባይሆንልኝ፣
አደባባይ ሰልፍ ወጣሁኝ።

አደርገው እይዘው ባጣ እጨህበት አለቅስበት፣
የታጋዮች ድምፅ ቢጠራኝ የቆራጦች የጀግኖች ሃሞት፣
ጠመንጃ ፊት በባዶ እጅ መፋጠጡ፣
ጥይትን በሩጫ ፍጥነት ማምለጡ፣
እንዳይቀርብኝ ጀግንነቱ፣
መትረየስን በጎራዴ መመከቱ፣
ቢጋባብኝ ብየ ፋኖነቱ፣
ድንጋይ መወርወር ባይሆንልኝ፣
የጨለመችውን የደም ፀሃይ የተጋራሁ እንዲመስለኝ፣
አደባባይ ሰልፍ ወጣሁኝ።

ከጀመሩት እርምጃ ሰንዝር እንኳን ፈቅ ሳይሉ፣
ኢትዮጵያን በኢትዮጵኛ ለኢትዮጵያ እንደማሉ፣
አገር ብለው በአገርኛ ለአገር ህብረት ለተሰዉ፣
ሰው ብለው በሰውኛ ለሰው ልጅ ነፍስ ለታገሉ
በአንገዛም ፅናታቸው ከጥይት ናዳ መሀል ለዋሉ፣
ከፈሰሰው የዘር ወረርሽኝ ኢትዮጵያዊነትን ሊያድኑ፣
ለታፈኑትና ለወደቁት ለቀደምና ላሁኑ፣
የደም ህመማቸውን ላለቅስ የአገሬን ሰማእታት፣
ፅናታቸውን ላስመዘግብ ከዝንተ አለም የጀግኖች ቤት፣
መኪና ማንደድ ባልችል የጭካኔ ቁስለኞችን መጎተት ባይሆንልኝ፣
በእምቢታው መሳተፉ አውቶቡስ ለመሰበር ባያድለኝ፣
አደባባይ ሰልፍ ወጣሁኝ።

የደም የፍትሁን ጎዳና ላከብር ተገድጄ የነፃነት ወጋገኑን፣
የፍትህ እሪታዉን ባንጠለጥል ብየ አርማዉን፣
የአገሬ ጎበዞች በደማቸው ያጠጡትን ባጥንታችው የካቡትን፣
ከፍ አድርጌ ብሰቅል ብየ የታሪክ ባንዲራውን፣
አየር ህዋ ጠፈሩ ኡኡታየን እንዲሰማኝ፣
አደባባይ ሰልፍ ወጣሁኝ።

ኩራዛቸውን አጥፍተው ካደፈጡት ወላጆች፣
በር ዘግተው እንዳይወጡ ከተዘጉት ህፃናቶች፣
የመከራውን ወላፈን ከጎናቸው ቆሜ ባልቀምስ፣
የአልቃሽን ሙሾ ሰምቼ እንባወቼን በጉንጩቼ ባላፈስ
ለጀግኖች ቀብር ባልወጣ ለሳልስቱ ልቅሶ ባልደርስ፣
ካፈጠጠው ጭካኔ ጋር ምን አይን ላይን ባልተያይ፣
የጀግኖቹን ፅናት ላከብር ሰልፍ ወጣሁኝ
ከፈረንጆች አደባባይ።



este_dar@yahoo.com